# 1 አባሪ ረ - ለተጨማሪ ቋንቋዎች ይዘቶች

## 1.1 "አትደውልብኝ" የውሂብ ጎታ ምንድን ነው?

"አትደውልብኝ" የሚለው የመረጃ ቋት ተገልጋዮች መደበኛ የስልክ እና የሞባይል ቁጥራቸውን ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ መመዝገብ የሚችሉበት አገልግሎት ሲሆን አገልግሎቱ ነፃ እና ሁሉንም የግብይት ጥሪዎች ለመዝጋት የመጣ እና ያለመ ነው።

የ"አትደውሉልኝ" የመረጃ ቋት ደህንነቱ የተጠበቀ የመረጃ ቋት ሲሆን ተጠቃሚዎች የስልክ ግብይት ጥሪ እንዳይደርሳቸው የሞባይል እና የመደበኛ ስልክ ቁጥራቸውን የሚመዘግቡበት፣ የሚፈትሹበት ወይም የሚያነሱበት፣ በመረጃ ቋቱ ውስጥ ቁጥር መመዝገብ ነጻ እና አንድ ጊዜ ብቻ እንዲደረግ የሚፈለግ ነው።

ከተመዘገቡ በኋላ የቁጥሩ ባለቤት ወይም በእሱ ምትክ የሆነ ሰው ቁጥሩን ካላስወገደው በስተቀር የስልክ ቁጥሩ በመረጃ ቋቱ ውስጥ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል።

የሸማቾች ወይም በአገልግሎት ተጠቃሚዎች ጥበቃ ህጉ ማንኛውም ነጋዴ ለተጠቃሚዎች የግብይት ጥሪ ማድረግ የሚፈልግ ስልክ ቁጥሮች በ"አትደውሉልኝ" የውሂብ ጎታ ውስጥ መመዝገባቸውን እንዲያጣራ ያስገድዳል። ከላይ ያሉት ቁጥሮች በመረጃ ቋቱ ውስጥ ከታዩ፣ ከጥቂት ልዩ ሁኔታዎች በስተቀር ህጉ የግብይት ጥሪዎችን ማድረግ ይከለክላል [ከ 15.4 መያያዣ ሊንክ ጋር]።

የሸማቾች ወይም የአገልግሎት ተጠቃሚዎች ጥበቃና ፍትሃዊ ንግድ ባለስልጣን የ"አትደውልብኝ" የመረጃ ቋት ባለቤት ነው።

የመረጃ ቋቱ መመስረት እና በነጋዴዎች ላይ የተጣለው ህጋዊ ግዴታ በሸማቾች ጥበቃ ህግ ክፍል 16 "ለ" እና 16 "ሐ" ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## 1.2 እንዴት መመዝገብ እንደሚቻል/ ይቻላል

የስልጠና ቪዲዮዎችን አገናኝ

### 1.2.1 የሞባይል ስልክ ወደ አትደውልብኝ ዳታቤዝ በጣቢያው በኩል እንዴት መመዝገብ እንደሚቻል ።

የሞባይል ስልክ ቁጥር ወደ አትደውልልኝ ዳታቤዝ መመዝገብ በጣም አጭር ሂደት መመዝገብ ይቻላል። መረጃዎን በመመዝገቢያ ቅጹ ላይ እዚህ ጠቅ ያድርጉ ማለትም ወደ [ወደ አስተዳደር ቅጹ አገናኝ አለ] ላይ ከሞሉ በኋላ ስርዓቱ የጽሑፍ ወይም የድምጽ መልእክት ወደ ተንቀሳቃሽ መሳሪያዎ የማረጋገጫ ኮድ ይልካል። ይህ ኮድ በድረ-ገጹ ላይ በቅጹ ላይ መፃፍ አለበት ።

በቃ! የሞባይል ስልክ ቁጥርህ አትደውልልኝ ዳታቤዝ ውስጥ በተሳካ ሁኔታ ተመዝግቧል። ከአሁን ጀምሮ፣ ከገበያ ጥሪዎች እንዳይደውሉበት ይጠበቃሉ።

### 1.2.2 መደበኛ ስልክ ወደ አይደውሉልኝ ዳታቤዝ በጣቢያው በኩል እንዴት መመዝገብ እንደሚቻል:

መደበኛ ስልክ ቁጥር ወደ አትደውሉልኝ ዳታቤዝ መመዝገብ አጭር እና ምቹ፤ እና እንዲሁም ባለ ሁለት ደረጃ ሂደት ነው።
በመጀመሪያ ለ"አትደውሉብኝ" አገልግሎት የምዝገባ ቅጹን በ [የመንግስት ቅጽ ላይ ያለውን አገናኝ እዚህ ጠቅ ያድርጉ ] ያስገቡ እና ዝርዝሮችዎን ይሙሉ።

ዳታው ቤዝ ወይም ስርዓቱ ወደ ስልክዎ ይደውላል። ስልኩን ሲያነሱ የምዝገባ ሂደቱ ስልኩን ቀላል እና ፈጣን በሆነ መንገድ መጠቀም ይቀጥላል።

በቃ! የርስዎ የስልክ ቁጥር በተሳካ ሁኔታ ወደ አትደውሉልኝ ዳታቤዝ ውስጥ ተመዝግቧል። ከአሁን በኋላ ከገበያ ጥሪዎች ይጠበቃሉ። ወደ አትደውሉልኝ ዳታቤዝ እንዴት በስልክ መመዝገበ ይቻላል?

ለአትደውሉልኝ አገልግሎት እንዴት መመዝገብ ይቻላል? አገልግሎቱ ሊቀበሉበት ካሰቡት ስልክ ማለትም ተመሳሳይ ስልክ በቀላሉ 1-800-071-171 መደወል ይችላሉ። የድምጽ ምላሽ ይመልስልዎታል። ከዚያ በኋላ የሚደውሉለት ስልክ ቁጥር መታወቁን እና ወደ ዳታ ቤዙን (ስርዓቱ) መግባቱን ያረጋግጡ። ጥሪውን እንዲያቋርጡ ይጠየቃሉ እና መልሶ ለመደወል ይጠባበቁ። ስልኩ ይደውላል፣ እና ይህን የስልክ መስመር ለአትደውሉልኝ አገልግሎት መመዝገብ እንደሚፈልጉ ማረጋገጥ ይችላሉ።

ተንቀሳቃሽ ስልክ ከሆነ - በመልእክቱ ውስጥ ኮድ በመጠቀም እራስዎን ማስወቅ ይችላሉ።

በቃ! ስልክ ቁጥርዎ ወደ አትደውልልኝ ዳታቤዝ ውስጥ በተሳካ ሁኔታ ተመዝግቧል። ከአሁን ጀምሮ፣ ከገበያ ጥሪዎች ይጠበቃሉ አይቀበሉምም።

### 1.2.3 ወደ እንዳትደውሉልኝ ዳታ ቤዝ በቻት ቦት እንዴት መመዝገብ እንደሚቻል

እንዲሁም ወደ አትደውሉልኝ አገልግሎት በዋትስ- አፕ ቻት መመዝገብ ትችላላችሁ። የኛን የዋትስ- አፕ ቻት ቦት በመጠቀም ወደ ቀላል እና ፈጣን ምዝገባ የሚወስድዎትን የሚከተለውን ሊንክ ይጫኑ። -እዚህ ጠቅ ያድርጉ

በቃ! ስልክ ቁጥርዎ ወደ አትደውልልኝ ዳታቤዝ ውስጥ በተሳካ ሁኔታ ተመዝግቧል። ከአሁን ጀምሮ፣ ከገበያ ጥሪዎች አይደወልሎትዎም ይጠበቃሉም።

## 1.3 የእኔ ስልክ ቁጥር በ "አትደውሉብኝ" የውሂብ ጎታ ውስጥ መመዝገቡን እንዴት ማረጋገጥ እንደሚቻል።

ቁጥሩን ለመመዝገብ ሁሉንም ዘዴዎች በመጠቀም የስልክ ቁጥርዎ በ "አትደውሉልኝ" የውሂብ ጎታ ውስጥ የተመዘገበ መሆኑን ማረጋገጥ ይችላሉ።

ቅጹን በመጠቀም [ከመንግስት ቅጽ ጋር በሚያገናኝ ማለትም ሊንክ እዚህ ጠቅ ያድርጉ]

- 1-800-071-171 በኩል በመደወል
- በዋትስአፕ በኩል [ከዋትስአፕ ቦቱ ጋር ማገናኘት ማለትም ሊንክ እዚህ ጠቅ ያድርጉ]

## 1.4 ስልክ ቁጥርዎን ከ"አትደውሉልኝ" ዳታቤዝ እንዴት ማስወግድ እንደሚችሉ

የስልክ ቁጥሮን በማንኛውም መንገድ በመጠቀም ስልክ ቁጥርዎን ከ "አትደውሉኝ" መዝገብ ውስጥ ማስወገድ ይችላሉ፡-

ቅጹን በመጠቀም [ከመንግስት ቅጽ ጋር የሚገናኝ ማለትም ሊንክ እዚህ ጠቅ ያድርጉ

- 1-800-071-171 በኩል በመደወል
- በዋትስአፕ በኩል [ከዋትስአፕ ቦቱ ጋር ማገናኘት ማለትም ሊንክ እዚህ ጠቅ ያድርጉ]

## 1.5 ቅሬታ እንዴት ማቅረብ እንደሚቻል

ከንግዱ ያልተፈለጉ የግብይት ጥሪዎችን ለማቆም ከጠየቁ በኋላ በ"አትደውሉልኝ" የውሂብ ጎታ ውስጥ ወደ ተዘረዘረው ቁጥር መቀበልዎን ከቀጠሉ፣

### 1.5.1 ስለ ምን ቅሬታ ማቅረብ ይቻላል?

የቁጥሩ መመዝገቢያ ከፀናበት ቀን በኋላ የደረሰው እና ከህግ በስተቀር የማይካተት ከሆነ የግብይት ጥሪ ስለደረሰዎት ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ።

### 1.5.2 ቅሬታ (አቤቱታ) እንዴት ማቅረብ እችላለሁ?

ቅሬታዎን በመስመር ላይ ያለውን የቅሬታ ቅጽ እዚህ ጠቅ ያድርጉ በመሙላት ወይም ወደ "አትደውሉልኝ" በስልክ ቁጥር 1-800-071-170 በመደወል ቅሬታ ሊያቀቡ ይችላሉ።

በአግባቡ መመርመር እንድንችል ስለ ቅሬታዎ በተቻለ መጠን ብዙ መረጃ መስጠት አስፈላጊ ነው።

### 1.5.3 ውጤታማ የሆነ ቅሬታ እንዴት ማቅረብ እንደሚቻል

ስለተቀበሉት ጥሪ የበለጠ መረጃ መስጠት በቻሉ መጠን መረጃው ለሸማቾች ጥበቃ እና ፍትሃዊ ንግድ ባለስልጣን የበለጠ ጠቃሚ ይሆናል።

ስለ የገቢያ ጥሪዎች ቅሬታ ሲያቀርቡ ጠቃሚ መረጃ የሚከተሉትን ያጠቃልላል።

- የጥሪው ጊዜ እና ቀን
- ጥሪው የደረሰበት ቁጥር
- የደወለው አከፋፋይ ስም
- የደወለው አከፋፋይ አድራሻ ዝርዝሮች
- በውይይቱ ውስጥ ምን አይነት ምርቶች እና/ወይም አገልግሎቶች ቀርበዋል።
- በጥሪው ወቅት በስልክዎ ላይ የሚታየው ቁጥር (ወይም ምንም ቁጥር እንዳልታየ የሚያሳይ መረጃ)

- ከጠራህ ነጋዴ ጋር ነባር ግንኙነት እንዳልዎ?

### 1.5.4 ቅሬታ ሳቀርብ ምን ይሆናል?

መረጃው በባለሥልጣኑ የቅሬታ ዳታቤዝ ውስጥ የሚቀመጥ ሲሆን ጉዳዩ በባለሥልጣኑ ቅድሚያ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ይከናወናል።

## 1.6 ቅጣት

አንድ አከፋፋይ ህጉን ተላልፎ ከተገኘ እና ወደ አትደውሉልኝ ዳታቤዝ ላይ የተዘረዘረውን የሞባይል ወይም መደበኛ ስልክ ቁጥር ከደወለ፤ ለድርጅቱ 46,080 አዲስ ሽቄል እንዲቀጣ ይገደዳል፤ እና እንዲሁም ኮርፖሬሽን ካልሆነ ደግሞ - በ 25,610 አዲስ ሽቄል መጠን እንዲቀጣ ይጠበቃል።.

## 1.7 በመረጃ ቋቱ ውስጥ ከተመዘገቡ በኋላ ማን እንዲደውልልዎ የተፈቀደለት

የሸማቾች ጥበቃ ህግ ስድስተኛው ማከያ ከህግ የተለዩትን ይዘረዝራል።

በመረጃ ቋቱ ውስጥ ወደተመዘገበው ቁጥር የርቀት ግብይት ጥሪዎችን የማድረግ እገዳው የሚከተለው ከሆነ ተግባራዊ አይሆንም።

1. ሸማቹ ከአሁን በፊት አነጋግሮት ከነበር ማለትም ካነጋገረው በኋላ ለሸማቹ የግብይት ጥያቄን የሚያነጋግር እና በጥሪ እንዲመለስለት የጠየቀ ነጋዴ፤ ሸማቹ እንደተገለጸው ሻጩ እንዲመለስለት ጠይቆት ከነበረ የማስረጃ ሸክሙ በአከፋፋዩ ላይ ነው።

2. ከሸማቹ ጋር የሚዛመድ አከፋፋይ በግብይት ጊዜ ውስጥ ለሸማቹ የግብይት ጥያቄን እና ያንን ግብይት በሚመለከት ፣ ውሎቹን ስለመቀየር (በዚህ በተለይ - የተፈቀደ ጥያቄ ነው)፤ የዚህ ዝርዝር ድንጋጌዎች የግብይት ጥያቄን በተመለከተ ሸማቹ በራሱ ተነሳሽነት በተፈቀደው ጥያቄ ማዕቀፍ ውስጥ ያለውን ግብይት ትክክለኛነት ለማራዘም ካልጠየቀ በቀር የግብይት ጥያቄን በተመለከተ ወይም ነባር ግብይትን ለማራዘም አይተገበርም። ሸማቹ የነባር ግብይቱን ትክክለኛነት ለማራዘም በራሱ ተነሳሽነት የጠየቀው የማረጋገጥ ሸክም በነጋዴው ላይ ነው። ለዚህ ጉዳይ "በሂደት ላይ ያለ ግብይት" - በጋዝ ተጠቃሚ እና በጋዝ አቅራቢ መካከል ያለውን የጋዝ አቅርቦት ግብይት ጨምሮ ይሆናል።

3. ሸማቹ ለእሱ የግብይት ግንኙነት ግልጽ እና የተለየ ፍቃድ የሰጠው አከፋፋይ፣ ይህ ስምምነት የተገልጋዩን ስልክ ቁጥር በመደወል ካልተገኘ፣ የተጠቀሰው ስምምነት በኤሌክትሮኒክ መንገድ ጨምሮ በተለየ የጽሁፍ ሰነድ ውስጥ መሰጠት አለበት። እና ከላይ የተጠቀሰው የግብይት ጥያቄ ስምምነት በሸማቹ እና በነጋዴው መካከል የሚደረገውን ማንኛውንም ግብይት ለመፈፀም ለመመስከር አለመሆኑ በዚህ ውስጥ ይብራራል። የተጠቀሰው ስምምነት ሸማቹ ከዚህ ቀደም ፈቃዱን ካልሰረዙ በቀር ግንኙቱ ለአንድ አመት የሚቆይ ሲሆን ህጋዊነቱ ሊራዘም የሚችለው ከላይ በተጠቀሰው መንገድ በተጠቃሚው ፈቃድ ሆኖ ቢበዛ አንድ አመት መሆን አለበት።

4. በራሱ ተነሳሽነት አከፋፋይን ያነጋገረ እና ከዚያ አከፋፋይ የግብይት ግንኙነት ለማድረግ ግልፅ ፍቃድ የሰጠው ሸማች፤ ፈቃዱ ለአንድ አመት የሚሰራ ይሆናል። ነገር ግን ሸማቹ በማንኛውም ጊዜ ፈቃዱን ማንሳት ይችላል። የሸማቹን ፈቃድ እና ተቀባይነትን በሚመለከት የማስረጃ ሸክሙ በነጋዴው ላይ ነው።

## 1.8 ግላዊነት

1. እ.ኤ.አ. ህዳር 24፣ 2020 ማሻሻያ 61 በሸማቾች ጥበቃ ህግ፣ 1981 ዓመተ ምህረት - (ከዚህ በኋላ፡ ህጉ) ታትሟል፣ ይህም የሸማቾች ጥበቃ እና ፍትሃዊ ንግድ ባለስልጣን (ከዚህ በኋላ፡ ባለስልጣን) የውሂብ ጎታ ያቋቁማል እና ያስተዳድራሉ ይላል። የሸማቾችን የግብይት ግንኙነት በአከፋፋዮች ለመገደብ የሚፈልጉ የሸማቾች ስልክ ቁጥሮች ይመዘገባሉ ወይም በእነሱ ምትክ የሆነ ሰው ይመዘገባል።

2. ማሻሻያው የተጠቃሚውን አንድ ወይም ከዚያ በላይ የስልክ ቁጥሮችን ከመረጃ ቋቱ ውስጥ የመመዝገብ ወይም የማስወገድ መብትን ያስቀምጣል። እንዲሁም አከፋፋይ በውስጡ ከተመዘገበው ሸማች ጋር የግብይት ግንኙነት እንዳይፈጥር ይከለክላል። ለዚሁ ዓላማ፣ የግብይት ጥያቄን ለማቅረብ ፍላጎት ያለው ነጋዴ በመረጃ ቋቱ ውስጥ ተመሳሳይ ቁጥር መመዝገቡን ለማወቅ ይፈለጋል።

3. በህጉ አንቀጽ 16 ለ(ሠ) መሠረት የሸማቾች ጥበቃ ደንቦች (የግብይት መጠይቆችን ለመገደብ ማከማቻ)፣ 2022 ዓ.ም (ከዚህ በኋላ፡ ደንቦቹ) ተሻሽለዋል፣ ይህም የስልክ ቁጥር በመረጃ ቋቱ ውስጥ መመዝገብ የሚቻልበትን መንገድ ይቆጣጠራል። ወይም ተወግዷል። እና አንድ ንግድ በመረጃ ቋቱ ውስጥ ስላለው መረጃ የሚጠይቅበት መንገድ ወይም የሚያስወግድበት መንገድ እና እንዲሁም ሊጠይቅበት ይየሚችል መንገድ ነው።

4. የውሂብ ጎታው ምዝገባው ስም-አልባ የተመዘገበ የግል ዝርዝሮችን ማስገባትን አያካትትም። አንድ ሸማች በመረጃ ቋቱ ውስጥ እንዲገባ የሚጠየቀው ብቸኛው መረጃ የግብይት ጥያቄዎችን ለመቀበል የማይፈልገው ስልክ ቁጥር ነው።

5. የመረጃ ቋቱ የሚተዳደረው በሸማቾች ጥበቃና ፍትሃዊ ንግድ ባለስልጣን ነው። አከፋፋዮች በመረጃ ቋቱ ውስጥ የተከማቸውን መረጃ በቀጥታ ማግኘት አይችሉም፤ እና የጥያቄያቸው መልስ ሊያገኙት የሚችሉት አከፋፋዮች በመረጃ ቋቱ ውስጥ በጥያቄዎች በማቅረብ ነው (ጥያቄያቸው ያከናውናሉ)።

   የማጠራቀሚያ (የመሰብሰቢያ) ምዝገባ፡-

1.1. በ 1981 ዓ.ም የግላዊነት ጥበቃ ህግ ክፍል 8 መሰረት የውሂብ ጎታ በመረጃ ቋት መዝገብ ውስጥ ተመዝግቧል።

1.2. ማጠራቀሚያው በባለሥልጣኑ ባለቤትነት የተያዘ ነው።

1.3 የውሂብ ጎታ ቁጥር፡ 700069679 ነው።

1.4. የመረጃ ቋቱ የደህንነት ደረጃ በግላዊነት ጥበቃ (የመረጃ ደህንነት) ደንቦች -2017 መሰረት በመካከለኛ የደህንነት ደረጃ የተጠበቀ ነው።

2. ስለ ደንቦቹ ጥሰት ቅሬታ ማቅረብ

የመተዳደሪያ ደንቦችን መጣስ ያጋጠመው ሸማች ስለ ጥሰቱ ቅሬታ 'ቅሬታ ቅጽ' በመጠቀም አቤቱታ ማቅረብ ይችላል።

የቅሬታ ቅጹ የባለሥልጣኑ ተወካዮች ቅሬታውን እንዲመረምሩ ለማስቻል የተነደፈ ሲሆን ተገልጋዩ የመለየት መረጃ (ስም፣ ስልክ ቁጥር፣ ወዘተ) መሙላት ያለባቸውን መስኮች ያካትታል።

ይህ መረጃ የውሂብ ጎታው አካል አይደለም እና በማንኛውም ደረጃ ወይም ቅጽ ላይ በመረጃ ቋቱ ውስጥ ጥያቄ ለሚያደርጉ ነጋዴዎች አይተላለፍም።

መረጃው የተጠየቀበት ብቸኛው አላማ የባለሥልጣኑ ተወካዮች ማመልከቻውን እንዲይዙ እና አስፈላጊ ከሆነ አመልካቹን አግኝተው ማነጋገር እንዲችሉ ነው።

3. ጥናቶች፡-

3.1. ባለሥልጣኑ የመረጃ ቋቱን አጠቃቀምና የሸማቾችን ቅሬታዎች አያያዝ በተመለከተ መደበኛ የዳሰሳ ጥናት ያካሂዳል።

3.2. የዳሰሳ ጥናቱ ዳታቤዙን ከተጠቀሙ በኋላ ወዲያውኑ ወደ ተመዝጋቢው ይላካል እና አጠቃላይ መረጃን፣ የስነ ሕዝብ አወቃቀር መረጃ (መረጃ በጂኦግራፊያዊ አካባቢ) እንዲሁም የውሂብ ጎታውን የመጠቀም ልምድ መረጃን ያካትታል።

3.3. የዳሰሳ ጥናቱ የተነደፈው፤ ባለሥልጣኑ ትክክለኛ እንዲሆንና የተጠቃሚዎችን ጥበቃና የመረጃ ቋቱን የመጠቀም ልምድ ለማሻሻል ነው።

3.4. የዳሰሳ ጥናቱን መመለስ ግዴታ አይደለም እና ለተጠቃሚው ውሳኔ ተገዢ ነው።

4. ከተጠቃሚው ጋር ግንኙነት መፍጠር

ባጠቃላይ ሲታይ ባለሥልጣኑ በክፍል 4 ላይ እንደተገለፀው የዳሰሳ ጥናቶችን ከመላክ በስተቀር የመረጃ ቋቱን ለመጠቀም ከሚጠይቁ ሰዎች ጋር ግንኙነት አይፈጥርም።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ቅሬታን ለማስተናገድ ወይም በተጠቃሚዎች ላይ ጥሰት የፈፀመውን የንግድ ሥራ ለማጣራት የባለሥልጣኑ ተወካዮች እርስዎን ለማግኘት የሚፈልጉ ሊሆኑ ይችላሉ።

5. በመረጃ ቋቱ ውስጥ ለተከማቸው መረጃ የመጋለጥ መብት ያላቸው ወገኖች፡-

መረጃው የሚተዳደረው በባለሥልጣኑ አማካኝ ሲሆን፤ መረጃውን ለማግኘት የሚጠይቀው ሰው በጥያቄ (የስልክ ዝርዝር በማቅረብ እና በመረጃ ቋቱ ውስጥ ያልተመዘገቡ የቁጥሮች ዝርዝር በመቀበል) የሚቀመጥ ነው።

5.1. አከፋፋዮች የመረጃ ቋቱን በግልፅ እና በነፃነት እንዲያስሱ አይፈቀድላቸውም። ስለዚህም በውስጡ ለተከማቸው መረጃ አይጋለጡም። ነገር ግን መረጃ የሚቀበሉት ከስልክ ቁጥሮች ጋር በተገናኘ በጠየቁት ጥያቄ አካል ነው።

5.2. ጥያቄው የቀረበለት የስልክ ባለቤት መሆኑን በሚያረጋግጥ አሰራር መሰረት አንድ ሸማች በእጁ ያለው ስልክ ቁጥር በዳታ ቤዝ ውስጥ መቀመጡን በማንኛውም ጊዜ ማረጋገጥ ይችላል።

## 1.9. ከላይ ለተጠቀሰው ወገን ባለሥልጣኑ በምርመራ፣ በህግ ሂደት እና በመሳሰሉት መረጃዎችን ከህግ አካላት ወደ ባለስልጣን መ/ቤቱ ማስተላለፍ ሲጠበቅበት የተጠየቀው መረጃ ህጋዊ ምርመራ ተደርጎለት ይተላለፋል።

## ጥያቄዎች እና መልሶች

### 1.9.1 ቁጥር መመዝገብ የሚችለው ማን ነው?

ቁጥር ለመመዝገብ የሚከተሉትን መሆን አለብዎት:

• 'የመለያ ባለቤት ወይም (ሒሳብ ያለበት)' - ለመመዝገብ የሚፈልገው ቁጥር ባለቤት የሆነ።
• 'ፍቃድ ያለው ወይም የተፈቀደ' - ለሌላ ግለሰብ ቁጥሮች የመመዝገብ ስልጣን የተሰጠው ግለሰብ። የቀጠሮ ማስረጃ በሕግ የተደነገገ መግለጫ ወይም የተረጋገጠ የውክልና ሥልጣን ቅጂን ሊያካትት ይችላል።

### 1.9.2 ስንት ቁጥሮች መመዝገብ እችላለሁ?

የመለያው ባለቤትነት ማረጋገጫ እስካላቸው ወይም ቁጥሩን ለመመዝገብ ስልጣን እስካላቸው ድረስ አንድ ሰው ሊመዘገብበት የሚችለው የቁጥሮች ብዛት ላይ ምንም ገደብ የለም።

### 1.9.3 በመረጃ ቋቱ ውስጥ ቁጥር ለመመዝገብ የሚያበቃበት ቀን አለ?

በንቃት ካልተወገዱ በስተቀር ቁጥርዎ በገንዳው ውስጥ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል።

### 1.9.4 የተመዘገበ ቁጥሬን እንዴት መለወጥ እችላለሁ?

በተመዘገቡት የስልክ ቁጥርዎ ላይ ለውጥ ካስፈለገ ቁጥሩን በፖርታል፣ አፕሊኬሽኑን፣ ቻቱን በመጠቀም ወይም በስልክ 1-800-071-171 በመደወል ቁጥሩን ማስወገድ እና አዲሱን ስልክ ቁጥር በመረጃ ቋቱ ውስጥ ማስመዝገብ ይችላሉ።

እንዲሁም በመስመር ላይ ቅጽ [እዚህ ጠቅ ያድርጉ] በመጠቀም ቁጥር መመዝገብ ይቻላል።

### 1.9.5 የግብይት ጥሪዎችን መቀበል እስካቆም ድረስ ለምን ያህል ጊዜ ነው?

በ"አትደውልልኝ" ዳታ ቤዝ ውስጥ በተሳካ ሁኔታ ከተመዘገቡ በኋላ አንድ ሸማች በ15 ቀናት መጨረሻ ላይ ከገበያ ንግግሮች ይጠበቃሉ ወይም አይቀበሉም።

### 1.9.6 ምዝገባው ተግባራዊ ከሆነ በኋላ አሁንም የግብይት ጥሪዎችን ቢቀበልስ?

ምዝገባው ተግባር ላይ ከዋለ በኋላ፤ አሁንም የግብይት ጥሪዎች የሚደርሱዎት ከሆነ፣ ለሸማቾች ጥበቃና ፍትሐዊ ንግድ ባለሥልጣን [ከቅሬታ ቅጹ ጋር የሚገናኝ ሊንክ በመጠቀም እዚህ ጠቅ ያድርጉ ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ።